# የውዝግብር ጉዞ---አንድ ወደፊት፤ ሁለት ወደ ጎን፤ አራት ወደ ኋላ

ሀማ ቱማ

በተወሰነ ሕዝብ አስተሳሰብ መሰረት የጉዞ ትርጉሙ ሆነ እምብርቱ  መነሻና መድረሻው ሳይሆን ራሱ ጉዞው ነው:: ከሩቅ ቢነሳም መዳረሻውን አያውቅም የሚሉም አሉ--ግን በደፈናው ጉዞው እስከተካሄደ  ፋይዳ ቢስ ነው ማለት አይቻልም ይላሉ::ወደ ገሀነም ሆነ መንግስተ ሰማያት/ጀነት/ መጓዝ ነው ቁም ነገሩም ተብሏል:: ጉዞ ሲባል የራሱ ልዩ ልዩ ፍልስፍና አለው ብንልም የተወናበደ ጉዞ ደግሞ ሄደ ሲሉ ባለበት እርገጥ፤ወደፊት ሲሉ ወደ ኋላ፤ገስገስ ሲሉት ባለበት ሶምሶማ፤ መጠቀ ሲሉት ተሸማቀቀ መሆኑ ግልፅ ሲሆን ምን ጉደ ፈላ ማለቱ ሲያንስ ነው:: የተያያዝነው የውዝግብር ጉዞ የጎንዮሽና የኋላው አይሎበት ባለንበት ለመቆም እንኳን ብዙ መፍጨርጨርና መሮጥን የግድ አድርጎብናል::

በሀገራችን የትግል ታሪክ የስድሳዎቹ ወጣቶችና ተራማጅ ኃይሎች ያካሄዱት ተጋድሎ አንድ እርምጃ ወደፊት ለመሆኑ የየካቲት አብዮት ምስክር ነው:: የነበረውን የገለማ ስርዓት ለማውደቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦን አድርጓል:: ይህ ትግልና አብዮት የተነሳባቸው መሰረታዊ ምክንያቶች ወይም ያነገባቸው ዴሞክራሲያዊ መርሆዎች በኢትዮጵያ ታሪክ-- ምንም እንኳን ቀደም ሲል የመፈንቅለ መንግስት ሙከራዎች የነበሩ ቢሆንም-- አዲሶች ነበሩ:: ሕዝባዊ መንግስት ይመስረት ፤ የብሄረሰቦችና የሀይማኖት  እኩልነት ይረጋጋጥ፤ መንግስትና ሀይማኖት የተለያዩ ይሁኑ፤ መሬት ለአራሹ፤ የላባደሩ መብት ይከበር፤ ዴሞክራሲ አለገደብ፤ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ይስፈን፤ ሉዓላዊነት ይከበር ወዘተ የሚሉት ሁሉ በጥቅሉ ያን ያበቃለትን ስርዓት ከነግሳንግሱና ኋላቀር አስተሳሰቡ ጠርጎ የሚያስወግድ ነበር ማለት ይቻላል:: ለዚህም ነው የየካቲት አብዮት ለሀገራችን ብሩህ ቀንና ተስፋን ያዘለ የሕዝብ አመፅ የነበረው:: ለዚህም ነው በዚያን ጊዜ የአድህሮት ኃይሎች ሀሉ ሊገቱት የተረባረቡበት:: የዚህ አብዮት ነፀብራቅ ሆኖ በሀገሪቷ በመጀመሪያ የፖለቲካ ፓርቲነትም ብቅ ያለው ኢሕአፓም ራሱ ከድርጅት አንፃር የወደፊት እርምጃና እመርታ መሆኑም ታይቷል:: በመሆኑም የደርግ ቡድን ሁለት እርምጃ ወደ ኋላ ሆኖ የአብዮት ቅልበሳን መርዶ አሰምቶን ይህንንም በሽብርና ፍጅት አጅቦ ሀገሪቷን ለጠባቦች አመቻችቶ ሰጥቷል:: በአንፃሩ ፀረ ደርጉ ትግል መፋፋሙ ወደፊት ጉዞ ሲሆን የጠባብ ድርጅቶች መከሰትና በደርጉ ፀረ ህብረ ብሄር ድርጅቶች ሽብርም ተጠቅመው መጠናከር መቻላቸው የኋልዮሽ ኋልዮሽ ጉዞ መሆኑም ታይቷል፡

አብዮት ወይም የሕዝብ ትግል ለጥ ባለና አስፋልት በፈሰሰበት ጎዳና የሚጓዝ አይደለምና ውጣ ውረድ አለበት ቢባልም የትግሉ ራሱ ጉዞው በውዥንብር የተንገዳገደ ከሆነ መጨረሻው አያምርም:: የዚያን ጀግና ትውልድ ተጋድሎ ለማርከስና ዴሞክራሲያዊ መርሆችን ለመደምሰስ ባመቻቸው ጊዜና ወቅት ሁሉ የአድህሮት ሀይሎች ሲጥሩ እንደቆዩ የምናውቀው ነው:: ሀገሪቷን እንደሚያጠቃት ረሀብ ጊዜና ዓመትን እየቆጠረ የሚመጣው ይህ የኋልዮሽ ጉዞ እምቢልታ በአሁኑ

ጊዜ እየተነፋ ለመሆኑ ደግሞ አከራካሪ ጉዳይ አይደለም:: በ1997 ምርጫ ወቅትና ዙሪያ የሕዝብ ትግል አንድ እርምጃ ወደፊት ሄዶ ከዚያ ግን በአፈናው የተነሳ ብቻ ሳይሆን በተፈፀሙ ስህተቶች ና የእንብርክና እጅ እንስጥ ባይ ጎራ በማየሉ የተነሳ ትግሉ ወደ ኋላ መነተቱ መጓዙ አልቀረም:: በአጠቃላይ ግን በለውጥ ፍለጋና በስልጣኔ ሽፋን፤ በድፍኑ ኢትዮጵያዊነት የሚል መፈክርን በማ ስተጋባት፤ የሕዝብን ብሶትና ንዴት በጠባቡ ቃኝቶ የሆነ ሕዝብን (ለወያኔ ኦሮሞውና አማራውን ወዘተ ለመሰሎቹ ደግሞ ትግሬውን በሞላ) በጠላትነት ፈርጆ ለማፋጀት በመጮህ፤ የድርጅቶችን ድክመት ለድርጅቶች አላስፈላጊነት ማጠየቂያ አድርጎ በማቅረብ ሕዝብን ድርጅት አልባ ለማድ ረግ በስልት በመስበክ፤ ግራ ቀኙን ረግጦ ግን ሁሌም የቀኝ ቀኝ ሆኖ፤በፈረደበት ኢሕአፓም ላይ በቀጥታና በእጅ አዙር እየዘመቱ ያሉትንና የገደል ማሚቶአቻቸውን በየፈርጃቸው ስንመረምር የኋልዮሽ ጉዞ መጀመሩን ሳይሆን ፍርጠጣ ደረጃ መድረሱን የሚያመለክተን ነው:: ያ ስንት ደም የፈሰሰለት ቅዱስና ብሩህ ዓላማ ሊቀለበስና ሊቀበር ጉድጓድ እየተማሰ ለመሆኑም ዓይን ያለው ሁሉ የሚያየው ነው:: የታሪክ ጃርቶች ከአዲስ አበባ እስከ ሮማ፤ ከዋሺንግተን እስከ ካናዳ ከጉድ ጓዳቸው ብቅ ብቅ ብለዋል::

በኋልዮሹ ጉዞ የመረሸው ክፍል የህብረተሰብን ይዘት ክዶ ሁሉንም በአንድ ደፍጥጦ የማቅረቡ ጥረት ዓላማው እንዲሳካ በአንድ በኩል ያን ለጭቁኖች ብሎ ጨቋኞችን የተዋጋውን ትውልድና ድርጅት መዝለፍና ተሳስቶ ሀገር አጠፋ ብሎ መወንጀል፤ የባዕድ ርዕዮት አመጣብን ብሎ መጯጯኹ ሲያስፈልገው በሌላ በኩል ደግሞ በአፍንጫችን ስር ያለውን የመደብ --አዎን የመደ ብ- ልዩነት በመካድ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ( ለአንዳንዶቹ ከትግራይ ሕዝብ በቀር) የኢትዮጵያዊነ ት አራማጅና ጠበቃ ተደርጎ እንዲወሰድ መጣር አለበት:: በመሆኑም ኢትዮጵያን በመውደድ ሽፋን፤ ባዕዳንን በመቃወም ሽፋን፤ የኢትዮጵያዊነት ሰንደቅ ሲውለበለብ ባዕድ የተባለን አስተሳሰ ብ በመቃወም ደረጃ (ማለትም መንገድ አዳሪውም የቦሌውም ከበርቴ በአንድና በእኩል ኢትዮጵ ያዊ ሊሆኑ አይችሉም የሚለውን በመሰረዝ) እየተገፋ ያለው አቅዋም በመሰረቱ ከብዙሃኑ ጥቅም ጋር በተፃረረ መንገድ የምርጦችን (ልሂቅ ይሉታል መሰል እነሱ) ጥቅም ለማስቀደምና የበላይነታ ቸውን ለማስፈን የሚካሄድ ዘመቻ ነው:: ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአንድና በእኩል ደረጃ የሚያንፀባ ርቀው ኢትዮጵያዊነት የለም፤ኖሮ አያውቅም፤ መቸም አይኖርም:: በእነ በላይ ዘለቀና መንግስቱ ንዋይ መሰቀል፤ በ አያሌ አርበኞችና ሀገር ወዳዶች መጨፍጨፍ የተረጋገጠ ሀቅ ከመሆኑ ሌላ ዛሬም ቢሆን የእነ እንቶኔ ኢትዮጵያዊነትና የሰርቶ አደሩ ኢትዮጵያዊነት አንድ ሊሆን አይችል ም:: ቀደም ሲል አፄውን በሚኒስቴርነት ያገለገለው፤ ለጠቅ አድርጎ የደርጉ ባለስልጣንና ቀይ ሽብር አራማጅ ሆኖ ከርሞ ዛሬ ታጋይ በሉኝ የሚለው፤ ግማሽ በላይ የኢትዮጵያን ሕዝብ በብሄ ረሰብና በሀይማኖት መለኪያ ኢትዮጵያዊነትን የሚነፍገው ሁሉ አለኝ የሚለው ኢትዮጵያዊነትና የሕዝብ ኢትዮጵያዊነት የሚመሳሰል አይደለም::

ኢትዮጵያዊነት ሲሉ ኢትዮጵያዊነት ስንል ማለቱ የግድ ሆኗልና አረንጓዴ ብጫ ቀይ እሸሼ ገዳዎ ባዩና እውነትም ለኢትዮጵያ የቆመውን ምን ይለየዋል የሚለውን መዳሰሱ ያስፈልጋል::

ማነው ኢትዮጵያዊ ማለቱ ኢትዮጵያዊነት ምንድነው ከሚለው ጋር ተዛምዶ መመርመር አለበት::ሁሉም በኢትዮጵያ የተወለደ ሰው ኢትዮጵያን ይወዳል፤ኢትዮጵያዊነትን ያንፀባርቃል ማለት አይቻልም:: ይህን ማለት የህብረተሰብን ሀቅና ሳይንሳዊ ትንተናን መሳትና ህልመኛ መሆን ነው:: ሀገር ወዳድነት ከውልደት በቀጥታ አይሰርፅም::ኢትዮጵያን እንወዳለን ያሉ ባለስልጣኖች ሀገሪቷን በእውነትም ወደው በነበር ያደረጉትን ሁሉ ባላደረጉ ነበር:: ለዚህም ነው የኢትዮጵያን ሕዝብ የፈጀው ኮለኔል በምንም ሚዛን ሀገር ወዳድና ኢትዮጵያዊነትን አንፀባራቂ ሊባል የማይችለው:: አሌ የሚሉ ካሉ ግምገማቸው ሌላ ነውና ኢትዮጵያዊነት ሲሉ ከእኛ በመሰረቱ የሚቃረን ነው ማለት እንችላለን:: ሕዝብን እየፈጁ፤ ኢትዮጵያዊውን እያስለቀሱ ኢትዮጵያን እንወዳለን የሚገባን ሊሆን አይችልም--ማጭበርብር ነውና :: ኢትዮጵያን ሀቀኛ ዜጋዋ ሲወዳት የራሱ ዚቅ አለው-ሕዝባዊነት፤ ሀቀኛ ሀገር ወዳድነት:: ሌሎች ደግሞ የሚወዷት ያው በራሳቸው ለራሳቸው ነው:: በድፍኑ የሁላችን ሀገር እንደሌለች ሁሉ (ኖራ በነበረማ እነሱ ሲደላቸው ብዙሃኑ ባልተሰቃየ) የሁላችን ኢትዮጵያዊነት የለም:: ኢትዮጵያዊነት ስንል ሲሉ ማለቱ የግድ የሆነውም ለዚህ ነው:: ኢትዮጵያዊነት ከህብረተሰቡ ክፍፍልና ካለው ስርዓትና የመደቦች አሰላላፍ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም:: ይህ ስለተባለ ሶሻሊዝም መጣ ብለው የሚጠረጥሩ ለመኖራቸው ግልፅ ነው:: ግን ሀቅና የሆነ ርዕዮት ተወራራሽ ከሆኑባቸው ይብላኝላቸው እንላለን:: በቀላሉ ለመጀመር የአዜብ ጎላና ባለቤቷ ኢትዮጵያዊነት መቸም በጥያቄ ቢገባ ከወያኔ ውጪ እግዚኦ የሚለን አይኖርም:: ለወያኔ ያደሩ ሆዳሞች / ይህን ብቁ ቃል በፖለቲካው መስክ ላስገቡት ምስጋና ይድረስና/ --አድር ባዮች፤ ከርሰአደሮች ወዘተ--ኢትዮጵያዊነት ቢሉ በአደባባይ ብንስቅባቸው አንወቀስም:: ከዚህ አልፎ ተርፎ ታግለን ያከሰምነውን ትምክህት፤እየታገልነው ያለውን ጠባብነት፤ኋላቀርነትና አድህሪነት አቅፈው በዚሁ መሰረትኢትዮጵያዊነት የሚሉንን ደግሞ የካቲት የቀበረው በአዲሱ ሚሌኒየም አያንሰራራም እንላቸዋለን::

ልጅን ሲወዱ ከእነ እንትኑ እንደሚባለው ሁሉ ሀገርን ሲወዱ ከእነ አሉታዊ ባህሏ የሚል የለም:: ባዕድ ሲመጣና ላሰለጥናችሁ ነው ሲል-- ለምሳሌ በሙሶሊኒ ወረራ ጊዜ-- ምንም እንኳን ጎጂ ልምዶችና ባህሎች ቢኖሩንም የባዕድ አራሚና አሰልጣኝ አንሻም በሚል ወግድ አሉት እንጂ ለጣሊያን ሴራ ሰለባ አልሆኑለትም-- ከጥቂቶች በስተቀር:: ይህ ራሱን የቻለ ጉዳይ ሆኖ በበኩላችን ኢትዮጵያን ስንወድ በሀገራችን የነበሩትንና ያሉትን መጥፎ ክስተቶች ሁሉ ኢትዮጵያዊ ብለን አይደለም:: በደፈናው ፍቅር በነበረማ አርሶ አደሩ ጪሰኛ ሆኖ ሲሰቃይ፤ ሕዝብ መብቱና እኩልነቱ ተክዶ ሲበደል፤ሀገር አንዴ ለአሜሪካ አንዴ ለሩስያ ስትሸጥ፤ መብት ሲነፈግና ሕዝብ ሲያለቅስ፤ ረሀብ ሲያጠቃን፤ ጎጂ ባህሎች ህፃናት ሴቶችን ሳይቀር ሲያሰቃዩ፤ ወዘተ ገበናችን ነው፤ ሀገራችን ናት ነው በሚል ዝም ብለን በተቀበልን ነበር:: ወያኔንም ኢትዮጵያዊ ብለን ሳይራራልን በራራንለት ነበር:: ግን ይህ አልሆነም:: ኋላቀሩን ስርዓት አጋልጠን ታግለናል:: ጎጂ ባህሎችን ተቃውመን እንሻሻል ብለናል:: የብሄረሰብና የሀይማኖት ልዩነት ይቁም ብለን ታግለናል:: ረሀብ መኖሩን ማጋለጥ ያዋርደናል ላሉትም ከሚሰቃየውና ከሚሞተው ሕዝብ ጎን እንጂ ከእናንተ " ሀፍረት" ጎን አይደለንም ብለናቸዋል:: ትምክህትና ጠባብነትን አውግዘናል::

የፈረንጅ ጫማ መሳሙን ውርደት ብለናል፡፡ ሀገራችን ዴሞክራሲ ያስፈልጋታል ብለን ድክመቷ ን ጠልተን ተችተናል፡፡ ስለ ወደድናትም ውድ ህይወታችንን ገብረንላታል፡፡ ኢሕአፓ የኢትዮጵ ያዊነት ምሳሌ ነው ስንል የሚቃወሙ ባይጠፉም ሀቁ ግን ይህ ነው፡፡ በአፄው ዘመን ተሿሚ አልነበርንም፡፡ የደርግ ባለስልጣን ወይ ደጋፊና አዳናቂ አልነበርንም፡፡ የወያኔ አጫፋሪና ሹመኛ አልነበርንም፤ለመሾምና ለመነገድም ጎነበስ ፀጥ ብለን ወደ ወያኔ አልነጎድንም፡፡ ታዲያ ከአንዱ ወይ ሌላው አገዛዝ ጋር የጨቀዩትና-- አንዳንዶቹማ የሕዝብ ደም ሲያፈሱ የነበሩት---ዛሬ በምን ተዓምር ነው ኢሕአፓን በኢትዮጵያዊነቱ ጥያቄ ሊያነሱበት የሚቃጡት? ኢትዮጵያዊነት ስንል ሀገርን ከዴሞክራሲያዊ ለውጥና ይዘት አቆራኝቶ የሚከሰተውን እንጂ መርገሚን ፀጋ ብሎ የሚ ውገረገረውን አይደለም፡፡ ሀገራችንን እንወዳታለን ግን መጥፎ ገፅታዋን አንወድላትም፡፡ዘረኝነት፤ ጠባብነት፤ ህፃናትን መዳር ማጋባት፤ ወንድም እህትን ባሪያ ማለትን፤ መብት ረገጣውን፤ ትምክህ ትን፤ ረሀቡን፤ የሴቶች እኩልነትን መካድን፤ የሀይማኖት ልዩነትን፤ ጎጂ ባህሎችን፤ ወዘተ አንወደውም ብቻ ሳይሆን ልንቀይረው የምንፈልገው ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ብዝበዛና ጭቆና የሰፈነባትን ኢትዮጵያ አንወዳትም--በሀገር ደረጃ ፍቅር ስላለን ግን ልንለውጣት እንሻለን፡ ኢትዮጵያዊ ማለት ምሁር፤ሀብታም፤ እንግሊዝኛ አዋቂ፤ በባዕድ ሀገር ነዋሪ፤ ለወያኔ አዳሪ፤ዶክተ ር ፕሮፌሰር፤አምባሳደር ጄኔራል፤ቦሌ ባለቪላ፤ ልሂቅ ወዘተ ተብዬው ብቻ ነው ስለማንልም እጁ የቆረፈደው፤መንገድ የሚያድረው፤ ላቡን አፍሳሹ ላባደር አርሶ አደር፤ ሰፊው ሰርቶ አደር ግሮ ጥሮ ነዋሪ ሕዝብ፤ መከራና ገፈቱን ተቀባዩ ዜጋችንን በቅድሚያና በዋናነት ኢትዮጵያዊ እንላለን ፡፡ ብዙሃኑ ስንልም እሷን እሱን ነው፡፡ ስለዚህም የኢትዮጵያዊነት ትርጉማችንን ሕዝብን መሰረት ያደረገና ያስቀደመ እንጂ እንዲያው በደፈናው በውልደት ከቱሉ ፎርሳ እስከ ሞዓ አንበሳ ያቀፈ ውን ውጥንቅጥ ሊሆን አይችልም፡፡ በተራ ቁጥር ሰማንያ ሚሊዮን መሆን እንቸላላን ግን ኢትዮጵ ያዊው ሲቆጠር ቢያንስ የወያኔው አረመኔ አገዛዝ አራማጆች፤ ተለጣፊዎቹና ቅጥረኞቹ ሁሉ የሚቀነሱ ይሆናሉ፡፡ መወለድ ቋንቋ ነው የተባለውም ቦታው በዚህ ይሆናል፡፡

ጎጂ ባህል የለንም፤ ገበናችን ይደበቅ፤ ስልጣኔ ፈረንጅነት ነው የሚሉትንም ልናስተናግድ አንችል ም፡፡ የዝቅተኝነት ስሜት ስለሌለንና በሀገራችንም ታሪክ ስለማናፍር ከሌላው ሕዝብ መማርን በበጎ እናየዋለን፡፡ ፔኒሲሊን በኢትዮጵያ በዘመነ መሳፍንት ጊዜ ተሰራ ማለትም የለብንም፡፡ እንደ ዜጋ የዝቅተኝነት ስሜት ያላቸው በኢትዮጵያ ያፍሩና ረሀብ አለ አትበሉ እስከማለት ይደርሳሉ፡፡ ጎጂ ባህል ሁሉ ገበናና የሚደበቅ ይሆንባቸዋል፡፡የክስተቶችን መደባዊ ይዘት ማስረዳቱ ስለሚሳና ቸውና ረሀብ መስፈኑ ለምሳሌ የሕዝብ ድክመት ሳይሆን የስርዓቱ መበላሸት መሆኑን ማስረዳት ስለሚያቅታቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተራብ አትበሉ ይሉናል፡ ሐጢያታችን ያመጣብን መከራ ነው ፀልዩ ብለው ሊሰብኩንም ይሞክራሉ፡፡ ከመላ አፍሪካ አንደኛ የሆነው የፊስቱላ ሀኪም ቤት በአዲስ አበባ መገኘቱ ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱትን በመዳር የሚመጣ ነው መባሉን አታንሱ የሚሉ እነዚሁ ናቸው፡፡ በየብሄረሰቡ መቀየር መከልከል ያለባቸው ባህሎች እያሉ የ “ሀገር” ናቸው አይነኩ ማለቱ ኢትዮጵያዊነት አይደለም፡፡ ተወደደም ተጠላም ሀገራችን ያለችበት

ዓለም ይዞታና ሂደት ይመለከታታል። የዓለም ሕዝብ ቅርስ ቅርሷ ነው። በኢትዮጵያዊነት ሽፋን ፀረ ዴሞክራሲ ባህሎችና አቅዋሞችን መሞሸር አንችልም፤ አይገባምም። ኢትዮጵያዊነት ዴሞክ ራሲያዊነት ነው፤ ፀረ አድሀሪነት ነው። ዕድገት ብልፅግናን ያቀፈ ክስተት ነው። የዘመነ መሳፍን ት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በአፍንጫችን ይውጣ ብንል ሀገራችንን ማፍቀር እንጂ መጥላት አይደለም። በባዕድ ሀገሮች ተደባልቀው እየኖሩ በአፋዊ ደረጃ ከለልተኛ ኢትዮጵያዊነትን ሰባኪ ዎች የአስመሳይ አስመሳይ ቢባሉ ተገቢ ነው። ወይ ፅንስ ሀሳቡ አልገባቸውም ወይም አውቀው ያደናግራሉ። ለዚህም ነው በኢትዮጵያዊነት ሽፋን ያን ለለውጥ የታገለ ትውልድና ድርጅት ሊያወግዙ የሚቃጡት ሁሉ አሳፋሪና ማፈሪያ ሆነው የሚገኙት።

ማነው ኢትዮጵያዊ የሀገር መለያ
ራቁት ተኝቶ ጋቢ የሚያሰጣ?
ማነው ኢትዮጵያዊ መለያ ምንለው
ህፃን ለጋብቻ አንቆ የሚድረው
በጅምላ ሕዝብንም ሚዘልፍ ሚያዋርደው
በብሄር በእምነት ጥላቻን ያዘለው
ራሱ ደንቁሮ ሕዝብን የሚንቀው?
ኢትዮጵያዊነትስ ትርጉሙ የት ላይ ነው
ትምክህትና ጥበት አዙሮ እየደፋው?
አረፋ ደፋቂው ግደል ፍጀው ባዩ
በክልል ሽንሽኖ የሚለው ተፋጁ
ብዙ አይደሉምና ድፈር ጨርስ ባዩ
የሩቅ ሀገር ፋኖ የቃላት ጦረኛ
ማነው ኢትዮጵያዊ በሀቅም አርበኛ?
ያን ያለፈ ትውልድ በትግል የወደቀን
ሌት ተቀን ሚከሰው ሀፍረት አልባ ቡከን
ይህ ነው ኢትዮጵያዊ ኋላቀር ማፈሪያ
ምን ፍዳ መጣባት በሀገር በኢትዮጵያ!

ከጥያቄውና "ስብጭቱም" ባሻገር ደግሞ ይህ ጎጂ የኋልዮሽ ሽምጠጣ የሚከስትበት ሌላ መንገድ በድርጅቶች ላይ ዘመቻውና የድርጅትን አስፈላጊነት መካዱ ነው። ይህ ዝንባሌ መልኬ አላማረም ብሎ አፍንጫን በካራ መቆራረጥ ዓይነት ይዞታን እያንፀባረቀ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም። ድርጅት አያሻም ሰበካው ካለፍንበት ሂደት ሲታይ በፅንስ ሀሳብም የኋልዮሽ ጉዞ ነው። ለዘመናት ለራሱ ሳይደራጅ የቆየው ሕዝብ በስድሳዎቹ ዓመታት መደራጀት ጀምሮ

በመታገል ምንም እንኳን ጠንክሮ የትግሉን ድል በየካቲት ማስከበር ባይችልም ትልቅ እመርታን አስመዝግቧል፡፡ የመደራጀት መብት እንዲከበር የደም ዋጋ ተከፍሏል፡፡ ዕድርም፤ዕቁብም፤ሰንበቴም ድርጅት ነውና ድርጅት ስንል ለስርዓት ለውጥ፤ ለመብት መከበርና ለህዝባዊ መንግስት የሚታገል የፖለቲካ ድርጅት ማለታችም መሆኑ ሊሳት አይገባውም፡፡ ገዢ ክፍሎች በራሳቸው ተደራጅተው (መንግስት ማለት ድርጅት ነውና) ሕዝብ ግን ጉልበቱ ተበታትኖ በድርጅት ሳይተሳሰር እንዲዋልል ማድረግ ይፈልጋሉ፡፡ ለዚህም ነው ተቃዋሚ ድርጅቶችን ለማፍረስ የሚጥሩት፤ ደም የሚያፈሱት፡፡ ትግል ከተባለ ሕዝብ መደራጀቱና በድርጅት ስር መታገሉ ለድል ዋስትና ነው፡፡ ግብታዊ ፍንዳታዎች በታሪክ ያላቸው ቦታ የሚናቅ ባይሆንም ዘላቂ ድል ግን ከመደራጀትና በድርጅት መልክ ከመታገል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የማይካደው ወቅታዊ ሀቅ በርካታ ድርጅቶች የተጣለባቸውን ተስፋ ሊያሟሉ አለመቻላቸው ነው፡፡ ይህን ሀቅ ግን በፅንፍ ለጥጦ የድርጅት ኩነናው ከመንገሱ በፊት አደብ ገዝቶ አዎንታዊውን ከአሉታዊው በማስተያየት ሚዛናዊ ግምገማ ለማድረግ መነሳቱ ተገቢ ነው፡፡ ድርጅቶችን የትግል አባዜ የያዛቸው አስመስለው በማቅረብ ድል አይፈልጉም የሚሉም ብቅ ብለዋል፡፡ ድልን የማይፈልግ ድርጅት የትኛው ነው? ትግል ምኞት ሆኖ? ስለዚህም ኢሕአፓ ለፖለቲካ ስልጣን አልበቃምና ትግሉ ውጤት አልባ ነው ብሎ መደምደሙ ጭራሽ ለ 34 ዓመት ሲታይ የቆየውን የፖለቲካ ለውጥና ከስልጣን መያዝ በመለስ የተገኙ ድሎችን አልረዳ ማለት ነው፡፡ ቅንጅትና ህብረት በተናጠልም ሆነ በጋራ ያስመዘገቡት ፖለቲካዊ ድልና ለረጅሙም ትግል ያደረጉት የንቃት አስተዋፅዖ በመከፋፈላቸው ወይም ዛሬ ሕዝብን ባበሳጨ ደረጃ በመገኘታቸው ሊሰረዝ የሚችል አይደለም፡፡ የድርጅቶች መከፋፋል ወይም የአንጃዎች መፈጠር በየራሱ ማጠየቂያ ያለው ቢሆንም ሁኔታው የኋልዮሽ ጉዞ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ በሌላ በኩል ግን ያመረቀዘ ቁስል ላይ ቆራጥ እርምጃ መውሰድ ወይም በጋንግሪን የተበላሸን እግር ቆርጦ መጣል ጤንነት መሆኑም ሊረሳ አይገባም፡፡ በመሆኑም የድርጅቶች ይዘት እንዳለ ሆኖ ህልውናቸውን በማንኳሰስ ወይም በመሰረዝ ድርጅትን በተልፈሰፈሰ ንቅናቄ ወይም ስብስብ ለመተካት መጣሩ ጠቀሜታው ለሕዝብ ትግል ሳይሆን ጠበቅ ብሎ ለተደራጀው ወያኔ ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህ ቀቢፀ ተስፋን የሚያንፀባርቅ የተሳሳተ ፀረ ድርጅት አቅዋም በንፁህ ልቦና ሊገፋ ቢችልም በአብዛኛው ግን በሕዝብ ጠላቶች--ይጠቅማቸዋልና--የሚቀነቀን ወይም ባባዕዳን የሚሸረብ ሴራ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ድርጅት ስንልም ምን ማለታችን መሆኑን ለማስረዳት ዳግም ማስፈለጉ  የሚካድ አልሆነም ጉዳዩን በሚገባው ጥሞና ስንመረምር ደግሞ የተደራጀን ጠላት ለመታገል በተፃራሪው በተገቢው መንገድ መደራጀት አስፈላጊ ነው፡፡ ድርጅት ስንል በሚገባ ተዋቅሮ፤ ሁኔታው በሚጠይቀው መንገድም ተዘጋጅቶና ተሳስሮ፤ሙያተኛነትንም አንግቦ የሚታገል ነው፡፡ አመራር ብቻ ሳይሆን በየፈርጁ ከላይ እስከታች ተዋቅሮ፤ በስርዓትና ህግና ደምብ እየተገዛ፤በመርህ ግብሩ ተሳስሮ የሚታገል ነው፡፡ የፖለቲካ ድርጅትና የፖለቲካ ንቅናቄ ለየቅል ናቸው፡፡ ሁለቱም እንደ ሁኔታው ቦታና ሚና ቢኖራቸውም የፖለቲካ ድርጅት የትግል መሪነትን ሚና ንቅናቄው

ሊወስድበት አይችልም። የሀገራችንን ሆነ የሌሎችን ተመክሮ ብንወስድ ንቅናቄ በተከሰተበትና ለድል በበቃበት ሁሉ ንቅናቄው በድርጅት መመራቱ የታወቀ ነው። በሀገራችን በ 1997 ለተከሰተው ድክመት ለምሳሌ ሕዝባዊ ንቅናቄው በድርጅት ባለመመራቱ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን። ቅንጅት የነበረ ቢሆንም አባላቱ ራሳቸው ይሉ እንደነበረው በ "መንፈስ" ና ንቅናቄ ደረጃ ስለነበረ የተዋቀረ ድርጅት ሆኖ በስልት (ማለትም አረመኔው ወያኔን ከመቋቋም አንፃር) ሊታገል ባለመቻሉ ሊጠቃ ችሏል። ጠበቅ ያለና የተዋቀረ፣ የተጠናከረ ድርጅት ኖሮ በነበር ምናልባትም የተወሰኑ ትግሉን ሊያኮላሹ ወይም ወያኔም በአንፃራዊ ጥንካሬ ጉዳት ሊያደርስ ባልቻለ ነበር። በምስራቅ አውሮጳ ለምሳሌ ህዝባዊ ንቅናቄ ከተባሉት ጀርባ የተዋቀሩ ቡድኖችና ድርጅቶች ነበሩ። የፖላንዱ ሶሊዳርኖሽ የሰራተኛውና የሕዝብ ንቅናቄ ቢባልም በሀገር ውስጥ የነበረውን ድርጅታዊ ማዕከል እነ ሲአይኤና ቫቲካን ረድተው አዋቅረውት ነበር። ለማንኛውም ያልተደራጀን ንቅናቄ ወያኔ ያው እንደተደራጀው ማጥቃቱ የማይቀር ነውና /ታይቷልናም/ ለመቋቋም የሚቻለው በድርጅት መልክ በመዘጋጀት ነው። ይህም ማለት በይፋና በምስጢር መደራጀትን በሚዛን ይዞ (ምስጢራዊ መዋቅርን ዋና ቦታ ሰጥቶ) መገኘት ያስፈጋል ማለት ነው። በ 1964 ዓ.ም. ኢሕአፓ የተቋቋመው እስከዚያ ሲታገል የነበረው የተማሪዎች ንቅናቄው ሚናው እንዳለ ሆኖ በከፍተኛ ደረጃ የሚታገልና የሚያታግል የፖለቲካ ድርጅት መኖሩ ወቅታዊና ወሳኝ ሆኖ በመገኘቱ ነው። የነበርንበት ሆነ ያለንበት ሁኔታ ደግሞ አፋኝ አገዛዞችን መጋተር የሚጠይቅ በመሆኑ በላላ መንገድ ወይም በተዝረከረከ አደረጃጀት ልናሸንፍ አንችልም። ተፈቅዶላቸው በህጋዊነት የሚታገሉትም ቢሆኑ ድርጅታቸውን ጠበቅ ማድረግና ሙያተኛ መሆናቸው አስፈላጊ ነው። ይህን በተመለከት ዝርዝሩ በዚህ ፅሁፍ ወይ መድረክ ሊቀርብ የሚገባ ው ባይሆንም ሀቅነቱ ግን የሚካድ አይደለም። የፖለቲካ ድርጅቶችን ትግል የሚያግዙ ንቅናቄዎ ችና የሲቪል ማህበራት መኖራቸው ጠቃሚ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ድርጅቶችን የሚተካ ወይም ሊሰርዝ የሚከጅል አደረጃጀት ወይ ንቅናቄ ለትግሉ አይጠቅምም።

ከዚህ በተያያዘም የሕዝብን ሚናና የጋራ አመራርን ጠቀሜታ በመሰረዝ ግለሰብን በቁንጮነት ለማንገስ የሚደረገውም ጥረት በዝምታ የሚታለፍ አይደለም። የጎበዝ አለቃና መሪ ከሚለው የልምድ አነጋገር ውጪ ለትግሉ ወሳኙ ሕዝብ መሳተፉ እንጂ አንድ ወሳኝ መሪ መገኘቱ አይደለ ም። የፊውዳልና የንጉሶች ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ባህላችንና የታሪክ ዘገባ ቅኝታችን/ማለትም ለግለሰብ ሁሉን ምስጋና የሚሰጠው/ ወደ አንድ መሪ ፍለጋ ቢሰደንም ይህ ተክለ ሰብ ግንባታን የሚያስቀድም ዝንባሌ መዘዙ ፀረ ዴሞክራሲ ለመሆኑ ብዙ ተመክሮ አለ ። ስታሊን ተባለ ማኦ፣ ኪም ኢል ሱንግ ተባለ ኤንቨር ሆጃ ለፓርቲዎች ቀና አሰራር እንቅፋት ሆነው በጣዖትነት ተሰይመው ጉዳት አምጥተዋል። በሀገራችንም ንጉሱ ምን አጠፉ በሰፈነበት ራሳቸውን ስዩመ መለኮት ይሉ የነበሩትና አምልኩኝ ሊሉ አንድ ሐሙስ የቀራቸው አፄ ሲወገዱ ወሮበላ የሆነ ሻለቃ በቦታቸው ተተክቶ ሳይውል ሳያድር ሁሉን አዋቂ ሊቀመንበር ተብሎ ጭፍን አምባገነንነ ትን ማስፈኑ በምሬት የምናስታውሰው ነው። የፀሐዩ ንጉስ የልጅ ልጅ የፈረንሳዩ ንጉስ አንገቱ በአብዮተኞቹ የተቆረጠው የነበረውን የግለሰብ አምልኮ ከሕዝብ አንጎል መንቅሎ ለማውጣትና

ተራ ግለሰብ መሆኑን ለማሳመን ነበር:: የአንድ መሪ በላይነት በአብዛኛው ውሎ አድሮ ዴሞክራሲን አፋኝ ክስተት መሆኑ ታይቷል:: በተቃዋሚ ድርጅቶችም ውስጥ በአመራር ያሉ ሁሉ ቦታና ሚዛን ተቀምተው የሆኑ ግለሰቦች ሊቀመንበር/ፕሬዚዳንት ተብለው ሲሰየሙ የሚከሰተው ዴሞክራሲ ሳይሆን አምባገነንነት ለመሆኑ ጥርጥር የለውም:: ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የሕዝብ ተሳትፎና የድርጅቶች የተጠናከረ ትግል ሊጠየቅ ሲገባው ችግሩ ግለሰብ መሪ / መሬት ወድቀን ጫማውን ስመን የምናመልከውና ሲዘባርቅ ሳይቀር ዕፁብ ድንቅ የምንለው / ባለመኖሩ ነው ብሎ መብከንከን ጊዜ ማጥፋትና ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ መሄድ ነው:: ዴሞክራሲን እናሰፍናለን የሚሉ ድርጅቶች በውስጣቸው ዴሞክራሲና የጋራ አሰራር መስፈን አለበት:: ወደፊትም ፕሬዚዳንት ወይ ጠቅላይ ሚኒስቴር የሚባሉ ግለሰቦች የሕዝብ አገልጋዮች እንጂ ግብዝ የሹም አውራ ዶሮዎች እንዳይሆኑብን ተገቢውን መከላከያ ከወዲሁ ማስፈን ይገባናል::

ለወያኔ ምሱ ዱላ ነው ሲባል የለም መላና መተቃቀፍ ይቅደም ያሉት ክፍሎች ዛሬም የኋልዮሹን ጉዞ በእልህ ተያይዘውት ብረት ያነሳን ሁሉ የተወገዘ ይሁን በማለት ትግልን ለማዳከም እየጣሩ ናቸው:: ሁሉም ማንነታቸውን ስለሚያወቅ እገሌ ማለቱ አላስፈላጊ ነው:: በሰላማዊ ትግል ሽፋን፣ ለአንዲትም ቀን ሻማ አብርተው ለተበደለውና ለተጋዘው ለታሰረው የጮኹ ይመስል፣ አንዲት ቀንም መብት ይከበር ብለው በወያኔ ቅጥረኞች ቆመጥና ሰደፍ የተቀጠቀጡ ይመስል፣ በማደናገሪያ ስልት ለአስመሳይ እስር ከመዳረግ ሌላ ሀቀኞቹ የደረሰባቸው ሰቆቃና መከራ ሳይደርስባቸው፣ ሰላማዊ ትግል ሰላማዊ ትግል ብለው በጩኸት በማደናገር ፣ወያኔ የከረቸመው የዴሞክራሲ በር በርገግ ብሏል እያሉ ሀሰት እየሰበኩ ወሳኝና አስፈላጊ የሆነውን የትጥቅ ትግል የጀመሩትን ያወግዛሉ:: የኋልዮሽ ጉዞ ! ይህን የሀሳዊ መሲህ ሚናቸውን ለመወጣ ትደግሞ የፈረደባቸውን ድርጅቶች ይጠልዛሉ:: የሚጠሉትን ኢሕአፓን እንተወውና ትላንት እንደ ሱናሚ ነው ብለው መረን በለቀቀ መንገድ ሲያሞግሱት የነበረውን ቅንጅት ዛሬ ሲያወግዙ ት ምንም ገደብ የላቸውም:: የነፃነት እመቤት ያሏትን ክረምት ሳያበቃ የመጎንበስ እቴጌ ብለዋታ ል:: በሌሎች ላይ የደረሰውም ውርጅብኝ የሚታወቅ ነው:: በፖለቲካው መስክ ያውም ለዘብተኛ ትችት ያቀረብነውን ሁሉ “ ተሳደባችሁ ” ተብለን ስንወቀጥ እንዳልነበረ ሁሉ ዛሬ የስድብ ስድብ ን መሪዎቻችን ባሏቸው ላይ ያዘንባሉ:: ይህ ሁኔታ ለትጥቅ አስፈቺዎች ቀዳዳ ከፍቶላቸው እነሆ በድፍረት እየተዘዋወሩ በወያኔ ላይ አታምፁ፣ ጠላት አትበሏቸው የሚለውን ሰበካ እያስደመጡ ናቸው:: በወያኔ ሽቀጥ ላይ ማዕቀቡ ለወያኔ በተጎነበሱ አደናጋሪዎችና የክህደት ሸቃጮችም ላይ ቢሆን ተገቢ ነው::

ቀደም እንዳልነው ድርጅቶች የሚጠበቀውን በተጠበቀበት ጊዜ ሊያከናውኑ ወይም ድል በድል ሊሆኑ አለመቻላቸው ማጠየቂያ ኖረው አልኖረው አበሳጭ መሆኑ የሚገመት ነው:: ሲከፋፈሉ ወሽመጡ የሚቆረጥ፣ ህብረት ቅንጅቶች ሲፈርሱ ተስፋው ከአፈር የሚደባለቅ ዜጋ በደፈናው

ሊፈረድበት የሚችል አይደለም። ይህን በተመለከተ ሊኖረን የሚገባው ግንዛቤ ግን ሚዛናዊነትን ይመለከታል። ያለፈ ታሪክን ስንቃኝና ስንገመግም ለምሳሌ በጥቁርና ነጭ ደረጃ የታሪክን ግራጫና ዥንጉርጉር ሂደት ለማየትና ለመፈረጅ ከተነሳን ውጤቱ አያምርም። የታሪክ ክንዋኔዎ ችን ከግለሰቦች ብቻ የማያያዙ ድክመት አለብንና አፄዎቹን ወይ በመቶ በመቶ ቀናነት አሊያም በዲያብሎስነት የመፈረጁ ስህተት አብሮን ቆይቷል። አፄ ቴዎድሮስ ሆኑ አፄ ዮሐንስና ምኒሊክ፤ አልፎም አፄ ኃይለሥላሴ ደግም ክፉም የሰሩ ነበሩና ግምገማችን ሚዛናዊ መሆኑ ተገቢ ነው። የታገልናቸውን አገዛዞች በተመለከተ በአብላጫው ሚናቸው መጥፎና ሕዝብን ጎጂ ስለነበረና ስለሆነ ትግላችን ተገቢ ነበር፤ነውም። ደጉና ክፉውን የመመዘን ልምድ ካለን ድርጅቶችም ቢሆኑ የሰሩትን ጥፋት ብቻ የማየቱ ዝንባሌያችን ቦታ አይኖረውም ማለት ነው። ህብረቶችና ቅንጅቶች ም ቢሆኑ ከአመሰራረታቸው ድክመት አዘል የነበሩ ቢሆኑም በተወሰነ ደረጃ ደግሞ ለትግሉ አስተዋፅዖ ማድረጋቸው የታየ ነው። ፅንፈኛ ወገዛው አላግባብ የሚሆነው ለዚህ ነው። ይህ የጅምላ ውግዘት በመሰረቱ ታሪክንም መርሳት ይሆናል። ታግለውና መስዋዕት ሆነው ያለፉትን ስም በማጥፋት የተካኑ የታሪክ ምስጦች ዛሬም ባይጠፉም ጨለንቆ በሚል የአድዋን ድል መሰረዝ ፤የአርበኞችን ታሪክ በሰበብ አስባቡ ማርከስ፤ የፀረ ደርጉን ትውልድ የደም ግብር መካድ ወዘተ መወገዝ ያለበት ነው። በተለይም ያለፈውን የታገለውን ትውልድ ለማጥቃት የሚራወጡት ወንጀለኞችና ሀገር ዋይ ዋይ ስትል ከገዳዮቿ ጋር የተቃቀፉ ከነበሩ ለመከላከል መነሳታችን ቀዳሚ ግዴታ ይሆናል። ድርጅቶች ድክመት አላቸውና አያስፈልጉም፤ ያለፈው ትውልድ በመታገሉ ሀገርን ጎዳ፤ የአንድነት ኃይሎች ሊተባባሩ አልቻሉምና ህልውና የላቸውም፤ ወዘተ ወዘተ በሚል የኋልዮሽ ጉዞ ጨኸት የወደፊት ጉዞን ለማነቅ መነሳቱ የሚጠቅም አይሆንም። ድክመትን ለማስወገድ ደግሞ ትኋኑ አስቸገረኝ ብሎ ቤትን የማቃጠልን “ መፍትሄ” ማቀንቀን ስህተት ይሆናል።

ጎዳናው ጥምዝምዝ ረጅም ቢሆንም
የደም ሀውልት ሆኖ ትግል ቢጠይቅም
ብሩህ ቀን ይመጣል አንጠራጠርም።

ይህ እምነት ነው ትግላችንን ወደፊት ሊገፋ የሚገባው። በዚህም በዚያም በሆነው ምክንያት የጎንዮሽና የኋልዮሽ ጉዞ ያብቃ። አንድ እርምጃ ወደፊት በሁለት እርምጃ ወደፊት ይታጀብ።